# በአዲስ አበባ በተመረጡ ሁለተኛደረጃ ት/ቤቶች የ10ኛ ክፍል ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ግምገማ

ግርማ ገብሬ እና ደረጀ ገብሬ

## I. መግቢያ

### 1. የጥናቱ መነሻ

የቋንቋ ክሂሎችን በመማር ሂደት ውስጥ ይበልጥ ፈታኙና አስቸጋሪው የጽህፈት ክሂል እንደሆነ በተግባር የተፈተኑ ልምዶችና ጥናቶች ይጠቁማሉ። በጽህፈት ክሂል ብቁ ሆኖ ለመገኘት በርካታና ተከታታይ ልምምዶችን ማከናወን ይጠይቃል። በልዩ ልዩ ሁኔታዎች ላይ የሚያተኩሩ ተደጋጋሚ የመጻፍ ሙከራዎች ካልተደረጉ በስተቀር በክሂሉ ምሉዕ ችሎታ ሊኖር እንደማይችል በዘርፉ ጥናት ያካሄዱ ባለሙያዎች የመሰከሩት፣ በልምድም የተረጋገጠ ጉዳይ ነው። ከዚህ ሀሳብ በመነሳት በ1998ዓ.ም. ወደኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት ተመድበው የመጡትን የመጀመሪያ ዓመት ተማሪዎች የመጀመሪያ ነጻ የጽህፈት ሙከራ ገጽታ አጥንተን ተማሪዎቹ ያላቸው ችሎታ ሀሳባቸውን በወጉ በጽሑፍ ለማስተላለፍ የማያበቃቸውና እጅጉን ከሚጠበቀው በታች መሆኑን የጥናታችን ውጤት አመላክቷል። ጥናታችን በቀረበበት ወቅት ወደሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች ተማሪዎችም ወርዶ እንዲጠና ሀሳብ በመሰንዘሩ የዚህ ጥናት መነሻ ሆኗል።

### 2. የጥናቱ ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ1999 ወደመሰናዶ ትምህርት ለመግባት የሚያስችላቸውን ፈተና ለመፈተን በዝግጅት ላይ ያሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ጽሕፈት ችሎታ አጠቃላይ ገጽታ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፤ በውስጡም የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ለመመለስ ይሞክራል።

ሀ. የተማሪዎቹ ሀሳብ የማደራጀት ችሎታ ምን ይመስላል?

ለ. የአረፍተ ነገር ቅንብርና ሰዋሰዋዊነት ምን ይመስላል?

ሐ. ሀሳባቸውን ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት በመምረጥ ረገድ ያላቸው ችሎታ ምን ገጽታ አለው?

መ. በፊደል አጣጣል፣ በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና በአጠቃላይ የጽሑፍ ተነባቢነት ደረጃ ተማሪዎቹ ምን ዓይነት መልክና ገጽታ ያለው ጽሑፍ ያቀርቡ ይሆን?

ሠ. በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ አድርገው ይሆን?

የሚሉ ናቸው።

### 3. ያጠናን ዘዴ

በዚህ ጥናት ውስጥ የተጠቀምንበት ዘዴ ገላጭና ዓይነታዊ የምርምር ሥልትን ነው። ይኸውም ተማሪዎቹ ያሉበትን ወቅታዊ መረጃ ለማግኘት የሚስችል ዘዴ በመሆኑ ነው። የመረጃ አሰባሰቡ ተማሪዎቹን በቀጥታ ድርሰት በማጻፍና

በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ትምህርት መማራቸውን እንዲሁም ልምምድ ማድረጋቸውን ለማወቅ የሚያስችል የጽሁፍ መጠይቅ በማስሞላት ነው፡፡ ጥናቱ በአስረኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ እንዲያተኩር የተደረገው ተማሪዎቹ የኢትዮጵያ ሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ ፈተና ለመፈተንና ወደመሰናዶ ለመሸጋገር ዝግጅት ላይ ያሉ በመሆናቸው ነው፡፡ ለጥናቱ የተመረጡትም የምኒልክ እና የቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺነት ናሙና አወሳሰድ ነው፡፡ በትምህርት ቤቶቹ ካሉት የአስረኛ ክፍል ምድቦች አድዳንድ ክፍሎችን በእጣ በመምረጥ፣ ከምኒልክ 56፣ ከቦሌ 51ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል፡፡ ሁሉም በቅድሚያ የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል (መጠይቁን ከአባሪ1 ይመልከቱ)፡፡ ከዚያም ከተማሪዎቹ ገጠመኝ ጋር የሚዛመዱ ሶስት አማራጭ የድርሰት መጻፊያ ርእሰጉዳዮች ተሰጥቷቸው አንዱን እንዲመርጡና ከ250 ቃላት በማያንስ ድርሰት እንዲጽፉ ታዞዋል፡፡ ርእሰጉዳዮቹ፣

1. ሴትን ልጅ ማስተማር ህብረተሰብን ማስተማር የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ወጣቱ ትውልድ ለምን የአውሮፓ እግር ኳስ አድናቂ ሆነ ?
3. የቤተሰብ ምጣኔ ጤናማ ህብረተሰብ ለመገንባት መሰረታዊ ጉዳይ ነውን?

የሚሉ ነበሩ፡፡

የተጻፈውን ድርሰትም በተመራማሪዎቹ በተሰናዳ መስፈርት ሁለት መምህራን እንዲያርሙት ተደረገ፤ የማረሚያ መስፈርቱ የሚያተኩርባቸው ነጥቦች ዋና ዋናዎቹ:- ውጤታማ አደረጃጀት፣ ውጤታማ ማስፋፊያ፣ ውጤታማ የአረፍተ ነገር ቅንብር፣ ውጤታማ የቃላት አመራረጥ ብቃትና አጠቃቀም እና ሥርዓተ ጽሕፈት የሚሉ ናቸው (አባሪ 2 ይመልከቱ)፡፡ ሁለቱ መምህራን የሰጡት ውጤት ተደምሮና ተካፍሎ አማካዩ ተያዘ (አባሪ 3 ይመልከቱ)፡፡ በነዚህ መረጃዎች ላይ በመመስረት ትንተናው ተሰጥቷል፡፡

## 4. የድርሰት / የጽህት ክሂልን ማስተማር

በጥንታዊ የቋንቋ ማስተማር ሂደት ውስጥ የጽህፈት ክሂል በክሂልነቱ ሳይሆን የሰዋሰው ማስተማሪያ መሳሪያ ሆኖ እንደቆየ ይገለጻል (Leki 1996, Richards 1990)፡፡ በጊዜ ሂደት በጽሁፍ ክሂል ላይ የሚደረገው ጥናት እድገት ስላሳየና ግልጽ ግንዛቤ እንዲኖር ስላደረገ እራሱን የቻለ የትምህርትና የምርምር አካል ሊሆን ችሏል፡፡ በዚህም የተነሳ መምህራንን እያሠለጠኑ ወደ ተግባር በሚያሠማሩ መንግሥታዊም ሆኑ ግላዊ ተቋማት ውስጥ የጽሕፈት ክሂል እንደ አንድ የሥልጠና ትምህርት አካል ሆኖ ይገኛል፡፡ በዚህ ረገድ በአንድ ቋንቋ አፊ ፊቶችንም ሆነ ኢ-አፊፊቶችን የሚያስተምሩ መምህራን ተማሪዎቻቸውን በተገቢው የጽሕፈት ችሎታ የተካኑና ሆነው እንዲገኙ መርዳት እንዲችሉ በስልጠናቸው ወቅት በጽህፈት ማስተማሪያ ዘዴ ላይ ያተኮሩ ኮርሶች ሊዘጋጁላቸው ሲሉ Kroll(1991,262) Leki (**1996**,**171**) ያስረዳሉ፡፡

ተማሪዎች በትምህርት ቤት ሕይወታቸው የሚማሯቸውን የተለያዩ አካዳሚያዊ የትምህርት አይነቶችን በተሳካ ሁኔታ ይከታተሉ ዘንድ የሕፈት ክሂላቸው

በሚያስተማምን ደረጃ ሊጎለብት ይገባል:: የፅሕፈት ክሂል ጎልብቶ መገኘት ወደፊት ለሚጠብቋቸው ሙያዎችና የስራ መስኮች ጠቃሚያቸው ነው:: የሥነ ጽሑፍ ባለሙያዎች ጋዜጠኞች፣ የታሪክ ተመራማሪዎችና፣ የሳይንስ ባለሙያዎች፣ መሀንዲሶች ወዘተ... ሁሉ ሙያቸው የሚጠይቀውን ሀሳብ በግልጽና በማየሻማ ሁኔታ ለሌሎች ለማስተላለፍና በሰነድነትም ቀርሶ ለማስቀመጥ እንዲችሉ የጽህፈት ክሂል መማርና መለማመድ ያስፈልጋቸዋል::

አብዛኛዎቹ ተማሪዎች በትምህርት ቤት ውስጥ የሚያሰናዷቸው ጽሁፎች ለመምህራቸው (በሳል መጣጥፎች፣ ወጎች፣ የቤት ስራዎች) ወይም ለራሳቸው (ማስታወሻዎች፣ ጭምቃሳቦች) የሚሰጡ ወይም የሚጻፉ ናቸው:: ከዚህ አኳያ ስንመለከተው የጽህፈት ችሎታ መኖር ተማሪዎች ትምህርቱን በተሳካ ሁኔታ ለመማር መቻላቸውን ማረጋገጫ ስለሚሆንላቸው በራሳቸው የመተማመን ችሎታቸውንም ያዳብርላቸዋል በማለት Richards (1990,100) ያስገነዝባሉ::

ጽህፈት ክሂል ጥቅሙ ከፍተኛ ሆኖ ሳለ ነገር ግን በአፍ መፍቻም ሆነ አፍ ባልፈቱበት ቋንቋቸው ለሚማሩ ተማሪዎች አዳጋች ሆኖ ይታያል:: Richards (1990,100) እንደገለጹት ጽህፈትን በወጉ መማር አሰልቺና የረጅም ጊዜ ልምምድን የሚጠይቅ በመሆኑ ተማሪዎችን ጭንቀትና ተስፋ መቁረጥ እንዲሰማቸው ያደርጋል:: በዚህም ምክንያት ብዙዎቹ ተማሪዎችም የጽህፈት ክሂልን አክብደው እንዲመለከቱት ይሆናሉ:: በሚያድርባቸውም አሉታዊ አመለከከት የተነሳ ትምህርቱን የሚያቋርጡ፣ ደካማ ውጤት የሚያስመዘግቡ ይኖራሉ፤ የተሳከ ውጤት ላይም የሚደርሱት ጥቂቶች ናቸው::

ጽህፈትን በወጉ ለመማር አስቸጋሪ ከሚያደርጉት ምክንያቶች ሌላው ከንግግር ጋር ያለው ልዩነት ይገኝበታል:: ንግግርን በማህበራዊ ግንኙነት መልመድ ሲቻል ጽህፈት ግን ሆን ብሎ አቅዶና አልሞ መማርንና መለማመድን ይጠይቃል:: አንባቢና ጸሀፊ በግንባር ተገናኝተው ሀሳብ የመለዋወጣቸው ሁኔታ ተናጋሪና አድማጭ ከሚኖራቸው ግንኙነት ጋር ሲተያይ ያለው እድል እጅግ ዝቅተኛ አብዛኛውን ጊዜም ፈጽሞ የማይገኝና የማይሳካ በመሆኑ ጽሁፉ በግልጽና በማያሻማ ቋንቋ መጻፍ ይኖርበታል:: ጸሀፊውም የአንባቢውን ማንነትና የሚጽፍበትን ርእሰ-ጉዳይ የተመለከተ የእውቀት ዳራ እንዲኖረው፣ ቢያንስ እንዲገምትና እንዲያብሰለስል የሚተጋ መሆንን ይጠይቀዋል (Richards 1990,101) ::

አንድ ጽሁፍም የአንባቢን ፍላጎትና ቀልብ ስቦ ተነባቢ እንዲሆን በአጻጻፉ ጥንቃቄ ሊደረግበት ይገባል:: Hairston (1986;6) እንዳሉት ውጤታማ የሆኑ መጣጥፎች (ኢ-ልቦለዳዊ ጽሁፎች) የሚከተሉት ስድስት መሰረታዊ ባህርያት አሏቸው:-

1. ጽሁፉ የሚያስፈልግበት ዐቢይ ነጥብ ያለው (አንባቢ አንድ ርእሰ ጉዳይ የሚያገኝበት ወይም የሚያውቅበት ) መሆኑ፤
2. ጽሁፉ ግልጽነት ያለው (ምን ለማለት ፈልጓል ብሎ መልእክቱን ለመረዳት
   አንባቢ ደግሞ ደጋግሞ በማንበብ እንዲቸገር የማያደርገው) መሆኑ፤
3. ጽሁፉ ወጥና መልካም ቅንብር ያለው (ብልጭ ድርግም የሚል የተበታተነ
   ሀሳብ ይዞ አንባቢውን የማያስቸግረው ) መሆኑ፤
4. የማያስፈልጉ ነገሮችን በማጨቅ የተንዛዛና ጊዜን የሚያባክን አለመሆኑ፤

5. አስፈላጊ የሆኑ ደጋፊ /የማጠናከሪያ ሀሳቦችን የያዘና የዳበረ መሆኑ፤
6. ጽሁፉ ሰዋሰዋዊ ተቀባይነት ያለው መሆኑ (በሰዋሰውና በስርአተ ነጥቦች
አጠቃቀም ምክንያት ስህተት የሚታይበት አለመሆኑ)፤

የሚሉ ናቸው :: እነዚህ ሁሉ ተዳምረው የጽህፈትን ትምህርት እጅግ አድካሚና ተፈታታኝ አድርገውታል ::

በሌላ በኩል ደግሞ ጽህፈትን ረቂቅ ጥበብ አድርገው የሚመለከቱት በርከታ ሰዎች መኖራቸው በክሂሉ ማስተማር ላይ አሉታዊ ጎን አስከትሏል :: Ede ( 1992 ;30-31) እንደ ገለጹት ብዙ ሰዎች፣ ‹ ጥሩ › የሚጽፉ ሰዎችን ልዩ ተሰጥኦ እንዳላቸው ከመቁጠራቸው የተነሳ ‹ ጥሩ › ለመጻፍ ችሎታ ያለው ሆኖ መወለድ ያስፈልጋል እስከማለት ይደርሳሉ :: ነገር ግን ሀሳብን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ ልዩ ተሰጥኦ ወይም ጥበብ ሳይሆን በመማርና በመለማመድ የሚገኝ ነው :: ይኸውም ጸሀፊዎች ጽሁፋቸው የተሳከ እንዲሆን ሚዛን የሚያነሳ ሀሳብ ላይ ያተኩራሉ፤ ያሰቡትን በትክክል የሚገልጹላቸው ቃላት ይመርጣሉ፤ የሀሳቡን ፍሬ ነገር ባካተተ ሁኔታ ያቀናብራሉ፤ ከአንባቢ የሚጠበቀውን ምላሽም ያስባሉ :: እንዲሁም፣ መግለጽ የሚፈልጉትንና የመረጡትን ሀሳብ በወረቀት ላይ በመነዳደፍ ወይም በአእምሯቸው ውስጥ በማብላላት ውጤታማ ሊሆን መቻል አለመቻሉን በመገምገም ወደጽሑፍ ይለውጡታል:: ስለዚህም ጽህፈት ምስጢራዊ የሆነ ጥበብ ሳይሆን የማቀድ፣ የማርቀቅና የመከለስ ብሎም የአርትኦት ሂደት በመሆኑ ይህንኑ ሥልት ማስተማር ይገባል ::

ተማሪዎችን ጽህፈት ለማለማመድና የሚያስፈልጋቸውን ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ የጽሕፈት ክሂል መምህራን የማስተማር ሥልጠናው፣ ልምዱና እውቀቱ ሊኖራቸው ይገባል :: ካልሆነ ግን በጽህፈት ማስተማር ሂደቱ ላይ አሉታዊ ጎን ይኖረዋል :: የእለት አዋዋላቸው በሚሠነዝርላቸው ተለምዷዊ በሆነ የማስተማሪያ ዘዴ የሚጠቀሙ መምህራን በክፍል ውስጥ የሚያሳልፉትን አብዛኛውን ጊዜ ቃላዊ ለሆኑ ተግባሮች ሲገለገሉበት ጽህፈትን ግን የክፍል ውጪ ክንውን አድርገው ይቆጥሩታል :: ይህ ሁኔታ ተማሪዎች የሚፈልጉትን ድጋፍ እንዲያገኙ ለማድረግ አመቺ አይደለም :: Hedge (1990 ;11) ፣ Kroll (**1991 ፤252)** እንደሚያስገነዝቡት ፣ መምህራን ተማሪዎቻቸው እንዲያቅዱ፣ እንዲያረቁና እንዲከልሱ የሚያስችላቸውን ተስማሚ የጽህፈት ክንውን በመፍጠር የክፍል ውስጥ ጊዜን ለጽህፈት መገልገል ይገባቸዋል :: ምክንያቱም ተማሪዎች በትኩረትና በንቃት በጽህፈት መሳተፍ የሚችሉት በክፍል ውስጥ የጽህፈት ልምምድ ሲያደርጉ ነው :: በቤት ሥራ ማሠራቱ ደካማ የተባሉ ተማሪዎች በራሳቸው ጊዜና ፋታ አግኝተው እንዲጽፉና በራስ መተማመንን ማዳበር እንዲችሉ ለመርዳት ታስቦ ሊሆን ይገባል ::

ከላይ ጠቅለል አድርገን እንደተመለከትነው የጽሕፈት ትምህርት ጉዳይ የተወሰኑ ወቅቶችና ክፍለ ጊዜዎች ተግባር ብቻ ሳይሆን ዘወትራዊና ያላሰለሰ ጥረትን የሚጠይቅ ነው፤ ከዚህ አኳያ ስናየው በአገራችን በሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች የሚማሩ ተማሪዎች በአማርኛ ቋንቋ ሀሳባቸውን በጽሑፍ የመግለጽ ችሎታ በተገቢው ደረጃ ላይ የሚገኝ አይመስልም:: በሁለተኛ ደረጃ ት/ቤቶች በሚገኙ ልዩ ልዩ ተማሪዎች ላይ

የተደረጉ ጥናቶች እንደሚጠቁሙት ክሂሉ ትኩረት ተሰጥቶት የሚሠራ ሆኖ አይታይም:: በልዩ ልዩ ደረጃ (በተለይ በሁለተኛ ደረጃና በኮሌጅ) ያሉ ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ብቃታቸው እጅግ አናሳና አሳሳቢ እንደሆነ ከሚጠቁሙ ጥናቶች ውስጥ ጥቂቶቹን መጥቀስ ይቻላል፤ (አለማዬሁ 1986፣ ክፍሌ 1986፣ ማረው 1987፣ ሰሎሞን 1987፣ ስዩም 1988፣ ግርማ 1990፣ ሰለሞን ዮሐንስ 1991፣ እንዳለ 1992፣ ጽጌ 1992):: እነዚህ አጥኚዎች የተማሪዎችን በአማርኛ ቋንቋ የመጻፍ ችሎታ የሚገኝበትን ገጽታ ከልዩ ልዩ አቅጣጫ መርምረዋል:: ከተማሪዎቹ ከግላቸው የጽህፈት ሙከራ፣ ከክፍል ውስጥ የጽሕፈት ትምህርት ምልከታ፣ ከመማሪያ- ማስተማሪያ መጻህፍት ይዘት፣ ቅንብርና ትኩረት፣ ከተማሪዎች የመማር ፍላጎትና ለቋንቋው ካላቸው ግምት አንፃር ተመልክተዋል፤ ከመምህራንም የማስተማር ብልሃትና አቀራረብ ዘዴ አንጻር መዝነዋል:: ከዚህ ሁሉ ክንውን በሁዋላ የደረሱበትን ማጠቃለያ ስንመለከት በመደበኛ ትምህርት ቤቶች የሚከናወነው የጽህፈት ትምህርት የተማሪዎችን የመጻፍ ብቃት ለማስገኘት በሚያግዝበት ደረጃ ላይ እንዳልሆነ ያለተዛንፎ የተስማሙበት እውነት ሆኖ አናገኘዋለን::

የችግሩን ስፋት፣ ጥልቀት፣ መጠንና አይነት ከጊዜ ክልል አንጻርም ስንመለከት ከዛሬ 30 በላይ አመታት ጀምሮ እየተባባሰ፣ እየጠለቀና እየሰፋ፣ እየተንሰራፋ መምጣቱን ጉዳዩ ያሳስባቸው የነበሩ መመህራንንም ያስጨንቅ የነበረ ጉዳይ መሆኑን እንረዳለን፤ (ነጋሣ 1965፣ ታደሰ 1979፣ አምሳሉና ደምሴ 1982፣ ተስፋዬ 1986፣ ባዬ 1987፣ ዮናስ 1991፣ ደረጀ 1998 ደረጀ ገብሬና ግርማ ገብሬ 1998):: ችግሩ ከትምህርት ቤት አልፎም በየእለቱ በሚያጋጥሙን ጋዜጦች፣ መጽሄቶችና መጻህፍትም ውስጥ በጉልህ እየታየ እንደሆነ የተጠቀሱት ተመራመራሪዎች የመሰከሩት ነው::

## 5. የመረጃ ትንተና

### 5.1. ከጽሁፍ መጠይቅ የተገኘ መረጃ ትንተና

| ቁጥር | ጥያቄዎች | ምላሾች በመቶኛ | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | | አዎንታዊ | | | አሉታዊ | | |
| | | ምኒል | ቦሌ | ድም ር | ምኒል | ቦሌ | ድምር |
| 1 | በዚህ አመት በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ አድርገሀል/ሻል? | 33.9 | 38.5 | 36.2 | 66.1 | 61.5 | 63.8 |
| 2 | ስለድርሰት አጻጻፍ የአማርኛ መምህርህ/ሽ አስተም ረውሃል/ሻል? | 100 | 92.3 | 96.3 | 0 | 7.7 | 7.7 |
| 3 | በዚህ አመት ድርሰት በግልህ/ልሽ ጽፈህ ታውቃለህ/ያለሽ? | 28.6 | 13.5 | 21.1 | 71.4 | 86.5 | 78.9 |
| 4 | በአማርኛ ድርሰት | 94.6 | 73.1 | 83.9 | 5.4 | 26.9 | 16.1 |

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| | የመጻፍ ፍላጎት አለህ/ሽ? | | | | | | |
| 5 | የድርሰት አጻጻፍ ስርአቶችን ማለትም ርእስ መምረጥ፣ ማጥበብ፣ ማርቀቅ፣ መከለስና ማረም ታውቃለህ/ሽ? | 50 | 59.6 | 54.8 | 50 | 40.4 | 45.2 |

የጽሁፍ መጠይቁ አምስት ጥያቄዎችን የያዘ በተማሪዎቹ የድርሰት ትምህርት፣ ልምምድና ፍላጎት ላይ የተመሰረቱ መረጃዎችን ለማግኘት እንዲያስችል ሆኖ የተዘጋጀ ነበር፡፡ መረጃ ሰጪዎቻችን ከዳግማዊ ምኒሊክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወንድ 18፣ ሴት 38 ፤ ከቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት ወንድ 27፣ ሴት 24 ነበሩ፡፡የአፍ መፍቻ ቋንቋቸው 96 ከመቶ አማርኛ ነው፡፡ የተገኘው መረጃ ቀጥሎ በሰንጠረዥ እንደተመለከተው ነው፡፡

ሠንጠረዥ 1፣ የጽሁፍ መጠይቅ ምላሽ

በድርሰት ትምህርት በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ ልምምድ ማድረግ በክሂሉ ጥሩ ደረጃ ላይ ለመድረስ እንደሚቻል በመስኩ ጥናት ካደረጉ አዋቂዎች የተገኘ ሀሳብ ያስረዳል፡፡ ይህንንም በክለሳ ድርሳኑ ላይ ከቀረበው መረዳት ይቻላል፡፡ በዚሁ መሰረት ከሠንጠረዡ ከቀረቡት መረጃዎች መገንዘብ እንደሚቻለው፣ በክፍል ውስጥም ሆነ ከክፍል ውጪ በአማርኛ ድርሰት በመጻፍ ልምምድ በማድረግ ረገድ የምኒሊክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 66.1 ከመቶ፣ የቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 61.5 ከመቶ አሉታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየውም የሁለቱም ትምህርት ቤት ተማሪዎች በድርሰት ትምህርት የሚያስፈልገውን ልምምድ አለማድረጋቸውን ነው ፡፡ ልምምድ አለማድረጋቸው ሊያስከትል የሚችለውን ውጤት በጻፉት ድርሰት ላይ ታይቶ ይሆን? ይህን ተማሪዎቹ ከጻፏቸው ድርሰቶች ትንተና በቀጣዩ ንኡስ ክፍል ማየት ይቻላል፡፡

በክፍል ውስጥ በአማርኛ መምህሮቻቸው የድርሰት አጻጻፍ ተምረው እንደሆን ለማወቅ ከቀረበው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ የምኒሊክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 100 ከመቶ፣ የቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 92.3 ከመቶ አዎንታዊ ምላሽ ሰጥተዋል፡፡ ይህ የሚያሳየውም በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎቹ በመምህሮቻቸው የድርሰት አጻጻፍ ትምህርት መማራቸውን ነው፡፡  መኪና አነዳድን በክፍል ውስጥ በጥቁር ሰሌዳ ላይ በሚቀርብ ገለጻ መማር እንደማይቻል ሁሉ የድርሰት አጻጻፍን ንድፈሀብ ስለተማሩ ብቻ ጥሩ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ ያዳብራሉ ማለት አይቻልም፡፡ በልምምድ መደገፍ ይኖርበታል፡፡

በመምህር ትእዛዝ ብቻ ሳይሆን በራስ ተነሳሽነትም ድርሰትን በመጻፍ ልምምድ ማድረግ በክሂሉ የተሻለ ደረጃ ላይ ለመድረስ ያስችላል፡፡ ተማሪዎች የሚጽፉትም በትምህርት ቤቶቻቸው ለሚገኙ ሚኒ ሚዲያዎች፣ ለጋዜጦች፣ ለመጽሄቶችና ለመሳሰሉት ሊሆን ይችላል፡፡ በዚህ ረገድ ያላቸውን ልምድ ለማወቅ ለቀረበው ጥያቄ ከምኒልክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤት 28.6 ከመቶ፣ ከቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ 13.5 ከመቶ አዎንታዊ ምላሽ ተሰጥቷል፡፡ ይህም ዝቅተኛ ውጤት ነው፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች አሉታዊ ምላሹ ከፍያለ ነው፤ ከሁለቱም ትምህርት ቤቶች ተማሪዎች 71.4 እና 86.5 ከመቶ አሉታዊ ምላሽ በተከታታይ ተሰጥቷል፡፡ ይህም ተማሪዎቹ የድርሰት ችሎታ ማዳበሪያ የሆነውን ሌላ አማራጭ መንገድ ያልተጠቀሙ መሆናቸውን ያሳያል ፡፡

ከውስጥ ያላቸው ተነሳሽነት ምንይመስላል ? በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት አላቸው ይሆን ? የሚለውን ለመለየት እንዲያስችል በአራተኛ ለቀረበው ጥያቄ ከተማሪዎቹ የተገኘው ምላሽ ደግሞ ከምኒልክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ 94.6 ከመቶ፣ ከቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ 73.1 ከመቶ ነው፡፡ ከዚህ መረዳት እንደሚቻለው የተማሪዎቹ በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት ከፍተኛ መሆኑን ነው፡፡ ነገር ግን ይህ ምላሽ በተራ ቁጥር ሶስት ከተሰጠው ምላሽ ጋር የሚቃረን ይመስላል፡፡ ውስጣዊ ፍላጎት ካላቸው ከክፍል ውጪ ድርሰት በመጻፍ ሊለማመዱ ለተለያዩ ክፍሎችም በመጻፍ ልምዳቸውን ሊያዳብሩ ይችሉ ነበር፡፡ ከፍላጎት የዘለለ መረጃ አልተገኘም፡፡

ጥሩ ድርሰት ለመጻፍ የድርሰት አጻጻፍ ሂደትን ማወቁና ተግባራዊ ማድረጉ ጠቃሚ ነው፡፡ ማቀድ፣ ማርቀቅ፣ መከለስ፣ ማረም፤ እነዚህን ሂደቶችም እንደድርሰቱ ግብ መቼነት ወደኋላና ወደፊት እየተመላለሱ መተግበር ጠቃሚ ዘዴ እንደሆነ የመስኩ አጥኚዎች የገለጹት ነው፡፡ ከዚህ ሀሳብ በመነሳት ለቀረበው አምስተኛው ጥያቄ የተገኘው ምላሽ ከምኒልክ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 50 ከመቶ ከቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ተማሪዎች 59.6 ከመቶ አንታ ምላሽ ነው፡፡ ይህም በጽህፈት ሂደት ላይ ያላቸው ግንዛቤም ሆነ የመተግበር ልምዳቸው በቂ አለመሆኑን ያሳያል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ ምላሾች ተያያዥነት ያላቸው ናቸው፡፡ በሁለቱም ትምህርት ቤቶች ያሉ ተማሪዎች በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ፍላጎቱ ያላቸው፣ ከመምህሮቻቸውም የንድፈሀሳብ ትምህርት ማግኘታቸውን የሚያመለክቱ ናቸው፡፡ ከዚህ ያለፈ ልምምድ ያላደረጉ መሆናቸውን መረጃው ያሳያል፡፡

የጽሁፍ መጠይቁ ምላሽ ከላይ እንደታየው ከሆነ ጽሁፎቻቸውስ ምን ይመስላሉ? ቀጥሎ በዝርዝር ይቀርባል፡፡

## 3. 2. የተማሪዎቹ ድርሰት እርማት ትንተና

ቀደም ሲል የትናቱን ዋና ዓላማና የጥናቱን ዘዴ ስንገልጽ እንደጠቆምነው የተማሪዎቹ ጽሑፎች የታረሙት በአምስት የጽህፈት መመዘኛ መስፈርቶች ነው (መስፈርቶቹ በአባሪነት ይገኛሉ)፡፡ የተማሪዎቹ ድርሰቶች እርማት አማካይ ውጤት ቦሌ 16.41 ምኒልክ፣29.05 ነው ፡፡ ይህ የእርማት ውጤትም የተማሪዎቹ በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል፡፡ መስፈርቶቹን መሠረት በማድረግ በአራሚዎቹ የተሰጠውን አማካይ ውጤት ይዘን ቀጥሎ ትንታኔውን በዝርዝር እናቀርባለን፡፡

### 3.2.1. ውጤታማ አደረጃጀት

ውጤታማ አደረጃጀት ሲባል የሚታዩት ዋና ዋና ነጥቦች የሀሳብ ወጥነት፣ ጠንካራ ዓላማ ያለው አጀማመር፣ አካሄድና አጨራረስ፣ ተገቢ የመሸጋገሪያ ሐረጎች አጠቃቀም፣ እንዲሁም ተገቢ የአንቀጽ አከፋፈልን የሚይዝ ነው፤ በዚህ ረገድ የተማሪዎቹ ጽሁፍ ገጽታ ኣማካይ ውጤት ዝቅተኛ ነው፡፡ ተገቢ አጀማመርም ሆነ አጨራረስ አይታባቸውም፤ ሀሳብን በአንቀጽ ከፋፍሎ በማቅረብም ረገድ ሁሉም ማለት ይቻላል እጅግ ደካማ ቅንብር የሚታይባቸው ናቸው፤ አብዛኞቹ ጽሁፎች (ከ250 ቃላት ባላነሰ ድርሰት ጻፉ የሚል ትእዛዝ ተሰጥቶ እያለ ) በአንድ አንቀጽ ብቻ ድርሰቶቹ ተጽፈው መቅረባቸው ሲታዩ ተማሪዎቹ ቀደም ባለው ትምህርታቸው ስለአንቀጽ አከፋፈልም ሆነ አስፈላጊነቱ በክፍል ውስጽ አግኝተናል ያሉት ትምህርታዊ ልምድ ውሸት ነው እንዴ ሚል ጥያቄ የሚያስጠይቁ ናቸው፡፡

ለአስረጅ፣ ቦ-02፣ ም- 21፣ ም-22፣


ቦ-02




### 3.2.2. ውጤታማ ማስፋፊያ

በዚህ ንዑስ መስፈርት ውስጥ የሚጠበቁ የጽሑፍ ባህርያት ሀሳብን በምሳሌም ሆነ በማስረጃ ማስደገፍ፣ ዝርዝር ማብራሪያዎች ማቅረብ፣ የሚነሱ ሀሳቦች ግልጽነትና የትኩረት ትክክለኛነት ናቸው:: በጥናቱ የተመረመሩት ጽሁፎች ሲታዩ ግን እንኳዋን የማስፋፊያ ስልትና ብልሃት ራሱ ሀሳቡ ያላቸው አይመስሉም:: ለምሳሌ ያህል የሚከተለውን የተማሪ ጽሁፍ ሙሉውን እንይ::

ምሳሌ፣ ቦ-15፣




ይህ ጽሁፍ ቀደም ሲል እንደተገለጸው የቤተሰብ ምጣኔ ያለውን ጠቀሜታ ማሳወቅ ዓላማው ያደረገ ነው:: ይሁንና፣ ሀሳቡን ሳይጀምር የሚጨርስ፣ እንደገና ደግሞ እያረፈ የሚነሳ የሚመስል፣ የሚነግረውን ነገር ቅደም ተከተል በውል ያልተረዳ በጥቅሉ ሀሳብን ደረጃ በደረጃ እያስፋፉ መሄድን ያልተረዳ ተማሪ ጽሁፍ እንደሆነ መገመት ይቻላል:: ይህንን ለአብነት ያህል እዚህ

ጠቀስነው እንጂ ሌሎቹም ጽሁፎች (ቦ-26፣ ቦ-05፣ ቦ-07፣ም-23…) ሁሉ አጠቃላይ ገጽታ ተመሳሳይ ነው።

### 3.2.3. ውጤታማ የአረፍተ ነገር ቅንብር

በዚህም ንዑስ መመዘኛ ሥር የሚነሱ ነጥቦች የአረፍተ ነገሮች ሰዋሰዋዊነት ማለትም የባለቤትና የማሰሪያ አንቀጽ ስምምነት፣ (የጊዜ፣ የቁጥር፣ የጾታ፣ የመደብ ስምምነትን) የሚመለከቱ ናቸው፤ አረፍተ ነገሮች የራሳቸው ወጥነት ብቻ ሳይሆን ከሌሎቹም አረፍተ ነገሮች ጋር ያላቸው ዝምድና ተጠየቃዊ መሆን ይገባዋል። የአንድ ሀሳብ ጥቅልነት የሚብራራባቸው አረፍተ ነገሮች ሥርዓታዊነት በእያንዳንዳቸው ላይ ብቻ የሚታይ ሳይሆን የእርስበርስም ቁርኝትና ትብብር እጅጉን አስፈላጊ መሆኑ ይታወቃል፤ ከዚህ አኳያ በዚህ ጥናት ውስጥ የተተኮረባቸው የተማሪዎች ጽሑፎች ሲታዩ እጅጉን ጉድለታም ሆነው ተገኝተዋል።

### 3.2.4. ውጤታማ የቃላት አመራረጥ ብቃትና አጠቃቀም

በዚህ ንዑስ መስፈርት ሥር የሚነሱት ዝርዝር ነጥቦች ቃላት፣ የሀሳብ ግልጽነትና ቁጥብነት የሚያገለግሉ፣ በሌላ አገላለጽ እቅጯዊ መልእክት የሚያስተላልፉ ሆነው እንዲገኙ ይጠበቃል። ምርምሩ በተካሄደባቸው የተማሪዎች ጽሑፎች ውስጥ ግን ይህ እውነት ፈጽሞ አይታይም። ይልቁንም ሀሳብ ከሚያስተላልፉ ቃላት ይልቅ የሚደበዝዙ ወይም ጨርሶውን የሚያጠፉ ዓይነት ሆነው ይገኛሉ። ለምሳሌ የሚከተለውን እንመልከት፤

ምሳሌ፣

ቦ-01 ፣ቦ-07፣ ም-23፣ ም-27፣


ቦ-01


ም-23

ይህ ጽሁፍ በተቻለ መጠን ተማሪው የጻፋቸውን ፊደሎች፣ ቃሎችና ነጥቦች እንዳሉ ለማሳየት ጥረት ተደርጓል፤ የተጠጋጉ፣ የማይነበቡ፣ ያላለቁ፣ አለቅርጻቸው የተጻፉ፣ ፈጽሞም አማርኛ የማይመስሉ አሉበት።

### 3.2.5. ውጤታማ ሥርዓተ ጽሕፈት

ይህ ንዑስ መመዘኛ የሚመለከታቸው ዝርዝር ነጥቦች የፊደል አጣጣል፣ የሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም፣ የህዳግ አጠባበቅና አጠቃላይ የጽሁፉን ገጽታ ለዓይን ግቡነት የመሳሰሉትን ነው። ከዚህ አኳያ ችግሩ የጠቅላላ ተማሪዎቹ ነው ማለት ይቻላል። በእያንዳንዱ ጽሁፍ ውስጥ ያሉ የፊደል ቅርጾችን ስንመለከት በፊደል ገበታ ላይ ካሉትና ከምናውቃቸው ጋር ፈጽሞ መምሰል ቀርቶ ባጠገባቸውም ያለፉ አይመስሉም፤

ምሳሌ፣ ቦ-02፣ ም-22፣ ቦ-24፣ ም-28


ቦ-24




ህዳግን በሚመለከት አብዛኞቹ ማለት ይቻላል ከጠርዝ እጠርዝ፣ ካናት እስከ ግርጌ የሚገኙ የወረቀቱ ክፍሎች በሙሉ ተገጥግጦባቸው ይታያሉ፤ አንዳንዶች ደግሞ ዝርው ድርሰት ሳይሆን ግጥም አስኪመስሉ ድረስ የወረቀቱን መሀለኛ ክፍል ይዘው ይቀርባሉ፤

ምሳሌ፣ ቦ-30




ወደ ሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀም ስንመጣ ግን በተገቢው ቦታ የገባ ነጥብ (ማየት እስኪናፍቅ ድረስ) ማግኘት አይቻልም:: በእጅ ጽሁፍ ውስጥ በቃልና በቃል መካከል ሁለት ነጥብ ማድረግ ወይ ባዶ ቦታ መተው የተገባ ነው:: ይሁንና እዚህ በርእሰ ጉዳይነት ይዘን የምንነጋገርባቸው የተማሪዎች ጽሁፎች ባንዱም ስልት የተካኑ አይደሉም:: ባዶ ቦታ የሚተውትን ስንመለከት አረፍተ ነገሩ የት እንደሚቆም መለያ ምልክት የላቸውም፤ ወይ ደግሞ ፊደሉን ከፊደል እያገጣጠሙ ቃል እንደሚመሠርቱት ሁሉ ሙሉውን አረፍተ ነገር፣ አንቀጽ ወይም ሙሉ ገጽ ላይ

የሚሰፍረውን ቃል ሁሉ እያቀጣጠሉና እያከታተሉ ይጽፉታል። በዚህም የተነሳ ጽሑፉን አንብቦ ለመረዳት አይቻልም፤ ወይም ትልቅ ፈተና ይሆናል።

አንጻራዊ በሆነ መልኩ የተሻሉ ከሚባሉት እጅግ ጥቂት ድርሰቶች

ምሳሌ፣ ም-13፣ ቦ-39


ቦ-39



**ማጠቃለያ፣**

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ1999 ዓ.ም. ወደመሰናዶ ትምህርት ለመግባት የሚያስችላቸውን ፈተና ለመፈተን በአዲስ አበባ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በዝግጅት ላይ ያሉ የአስረኛ ክፍል ተማሪዎች የአማርኛ ጽሕፈት ችሎታ አጠቃላይ ገጽታ ምን እንደሚመስል መመርመር ነው፤ በውስጡም የሚከተሉትን ዝርዝር ጥያቄዎች ለመመለስ ሞክሯል::

ሀ. የተማሪዎቹ ሀሳብ የማደራጀት ችሎታ ምን ይመስላል?

ለ. የአረፍተ ነገር ቅንብርና ሰዋሰዋዊነት ምን ይመስላል?

ሐ. ሀሳባቸውን ለማስተላለፍ የሚጠቀሙባቸውን ቃላት በመምረጥ ረገድ ያላቸው ችሎታ ምን ገጽታ አለው?

መ. በፊደል አጣጣል፣ በሥርዓተ ነጥብ አጠቃቀምና በአጠቃላይ የጽሑፍ ተነባቢነት ደረጃ ተማሪዎቹ ምን ዓይነት መልክና ገጽታ ያለው ጽሑፍ ያቀርቡ ይሆን?

ሠ. በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ አድርገው ይሆን?

የሚሉ ነበሩ ::

አላማውን ከግብ ለማድረስ ለጥናቱ የተመረጡትም የምኒልክ እና የቦሌ አጠቃላይ ሁለተኛ ደረጃ ትምህርት ቤቶች በአመቺነት ናሙና አወሳሰድ ነው። በትምህርት ቤቶቹ ካሉት የአስረኛ ክፍል ምድቦች አንዳንድ ክፍሎችን በእጣ በመምረጥ፣ ከምኒልክ 56፣ ከቦሌ 51 ተማሪዎች በጥናቱ ተካተዋል። ሁሉም በቅድሚያ የተዘጋጀውን የጽሁፍ መጠይቅ እንዲሞሉ ተደርጓል። ከዚያም ከተማሪዎቹ ገጠመኝ ጋር የሚዛመዱ ሶስት አማራጭ የድርሰት መጻፊያ ርእሰጉዳዮች ተሰጥቷቸው አንዱን እንዲመርጡና ከ250 ቃላት በማያንስ ድርሰት እንዲጽፉ ታዘዋል። ርእሰጉዳዮቹ፣

1. ሴትን ልጅ ማስተማር ህብረተሰብን ማስተማር የሚሆነው እንዴት ነው?
2. ወጣቱ ትውልድ ለምን የአውሮፓ እግር ኳስ አድናቂ ሆነ ?
3. የቤተሰብ ምጣኔ ጤናማ ህብረተሰብ ለመገንባት መሰረታዊ ጉዳይ ነውን?

የሚሉ ነበሩ።

ተማሪዎቹ የጻፏቸው ድርሰቶች በሁለት የድርሰት መምህራን ታርመውና ተተንትነው እንዲሁም ከጽሁፍ መጠይቁ ከተገኘው ምላሽ የተደረሰበት ግኝት ተማሪዎቹ በአመቱ የትምህርት ሂደታቸው ምንም አይነት የጽህፈት ልምምድ እንዳልነበራቸው የሚጠቁም ሆኖ አግኝተንዋል። ይኸውም፤ የድርሰት ርእስን የመወሰን፣ በአንቀጽ ከፋፍሎና አደራጅቶ የመጻፍ፣ ሀሳብን የማስፋፋት፣ ስርአተነጥቦችን ለይቶ በተገቢ ቦታቸው የመጠቀም ችግሮች ጎልተው ታይተዋል። የተማሪዎቹ ድርሰቶች እርማት አማካይ ውጤት ቦሌ 16.41፣ ምኒልክ 29.05 ነው ። ይህ የእርማት ውጤትም የተማሪዎቹ በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ችሎታ በዝቅተኛ ደረጃ ላይ እንደሚገኝ ያመለክታል።

### ይሁንታ፤

በይሁንታነት የምናቀርበው አንድ ጥቅል ሀሳብ ብቻ ነው- የድርሰት ትምህርት (የጽህፈት ክሂል) በንድፈሀሳብ ብቻ የሚጨብጡት ችሎታ ሳይሆን ያላሰለሰ ልምምድን የሚሻ ነው። ስለዚህም ተማሪዎቹ በተቻለ አቅም የጽህፈት ልምምድ ቢያደርጉና ከመምህራቸውም ተከታታይ እገዛ ቢደረግላቸው የተሻለ ይሆናል፤ የሚል! ለዚህም በየትምህርት ቤቶቹ ሁኔታዎች ሊመቻቹ ይገባል እንላለን።

### ዋቢዎች:-


ማረው ዓለሙ፤ 1987፤ «በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሁፍ ክፍል በ2ኛ ኣመት ተማሪዎች በግልና በቡድን የሚጻፉ በሳል ድርሰቶች ግምገማ ንፅፅራዊ ጥናት»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ሰለሞን ዮሐንስ፤ 1991፤ «የተማሪዎች የአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ስትራቴጂና የመምህራን የማስተማር ዘዴ ተጣጥሞ»።

የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ሰሎሞን ተሰማ፤ 1987፤ «የብጤ እርማት ተግባራዊነትና ውጤታማነት በ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተካሄደ ጥናት»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ሰይድ መር፤ 1993፤ «በዘጠነኛ ክፍል አማርኛ መማሪያ መጽሀፍ የቀረቡትን የጽህፈት ትምህርት ይዘቶችና ክንውኖች የማስተማሪያ ስነ ዘዴ ትግበራ (የመማር ማስተማር ሂደት) ግምገማ በሰባት የአዲስ አበባ ትምህርት ቤቶች ናሙናዊ ጥናት»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ስዩም ከበደ፤ 1988፤ «ድርሰትን በሂደታዊ ዘዴ በዘጠነኛ ክፍል ማስተማር ያለው ተግባራዊነት»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ታደሰ ሣህሌ፤1979፤ «የአዲስ አበባ 11ኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ጽሑፋዊ ባህርይ»። የአርት ባችለር ዲግሪ ለማሟላት የቀረበ ጽሑፍ፤ ለኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍል፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ነጋሳ እጀታ፤ 1965፤ «በ1962 ዓ.ም. በሁለተኛ ደረጃ መልቀቂያ የአማርኛ ፈተና ላይ በተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚታዩ የስህተት ዓይነቶች»። የአርት ባችለር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ።

አምሳሉ አክሊሉና ደምሴ ማናህሎት፤ 1982፤ *ጥሩ ያማርኛ ድርሰት እንዴት ያለ ነው?* አዲስ አበባ፤ ኩራዝ አሳታሚ ድርጅት።

አለማየሁ ፀጋዬ፤ 1986፤ «በዘጠነኛ ክፍል ተማሪዎች ድርሰት ውስጥ የሚፈጸሙ ዋና ዋና የስህተት ዓይነቶችና ዋና ዋና የስህተት ምንጮች ትንተና»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

እንዳለ ተስፋዬ፤ 1992፤ «በተማሪዎች ድርሰት ላይ የመምህራን ጽሁፋዊ መጋቤ ምላሽ»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ክፍሌ ሀብተ ማርያም፤ 1986፤ «የ11ኛ ክፍል ተማሪዎች ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ችሎታ»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

ዮናስ አድማሱ፤ 1991፤ «ሥነ ጽሑፍ በቋንቋ ጥናትና ትምህርት ሊኖረው የሚችለው ሚና/ችግሩ ምንድን ነው?» *የቋንቋዎች ጥናት ተቋም ዘጠነኛው ዓመታዊ ጉባኤ ፕሮሲዲንገስ*፣ ዘሪሁን አስፋውና ደረጀ ገብሬ (አርታእያን)፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ (ገጽ 119 - 124)።

ደረጀ ገብሬ፤ 1998፤ «የአራተኛ ክፍል ተማሪዎች በደረጃው የሚጠበቅባቸው በአማርኛ ሀሳባቸውን በጽሁፍ የመግለጽ ብቃት አላቸው? በሦስት የአዲስ አበባ ት/ቤቶች የተደረገ ናሙናዊ ጥናት»። ለኢትዮጵያ የትምህርት ጆርናል የቀረበ።

ደረጀ ገብሬና ግርማ ገብሬ፤ 1998፤ «በ1998 ዓ.ም. ወደ ኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነ ጽሑፍ ክፍለ ትምህርት አዲስ የተመደቡ ተማሪዎች የመጀመሪያ ጽሑፍ ገጽታ»፤ ለአስራ ስምንተኛው የቋንቋዎች ጥናት ጉባኤ የቀረበ።

ግርማ ገብሬ፤ 1990፤ በአማርኛ ድርሰት የመፃፍ ክሂልን ለማዳበር የመስተጋብር ስልት (Interactive approach) ያለው ተግባራዊነትና ውጤታማነት/በሀድያ ዞን የካቲት

25/26 ከፍተኛ ሁለተኛ ደረጃ ት/ቤት 10ኛ ክፍል ተማሪዎች ላይ የተሞከረ ጥናት፤ የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።
ፅጌ ታፈሰ፤ 1992፤ «ለጽህፈት ክሂል የተመረጡት የቋንቋ ትምህርት ይዘቶች እንዴት ተደራጅተዋል? በአዲስ አበባ መስተዳድር ትምህርት ቢሮ ለመጀመሪያ ደረጃ የሁለተና እርከን (5 - 8) በተዘጋጁት የአማርኛ መጻህፍት ላይ የተደረገ የይዘት ትንተናና ግምገማ»። የአርት ማስተር ዲግሪ ማሟያ ጽሁፍ፣ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ።

Brown,H.D.. Teaching by Principles: An Interactive Approach to Language Pedagogy. Englewood Clifts, N.J.:Prentice Hall Regents, 1994.

Byrne, D.. Teaching Writing Skills (New Ed.5th imp.). London and New York: Longman Group, 1991.

Cohen, A.D. and M.C. Cavalcanti.. "Feedback on Compositions: Teachers and Student Verbal Reports. "In:B.Kroll(Ed.). Second Language Writing (PP.155-177). Cambridge: CUP, 1993.

Ede, L. Work in Progress: A Guide to Writing . New York : W.W.Norton& Company, 1992.

Hairston,M. Contemporary Composition (4th Ed.). Boston: Houghton Mffin Company, 1986.

Hedge, T. Writing . Oxford University Press, 1990.

Hillocks, G.Jr. Research on Writing Composition: New directions for teaching. Urbana, Ill.: NCRE/ERIC , 1986.

Kroll,B. "Teaching Writing in the ESL Context. " In: M.Celce-Murcia (Ed.2nd Ed.). Teaching English as a Second or Foreign Language (PP. 264-76), 1991.

__________. "What does time buy ? ESL Student Performance on Home Vs Class Compositions" In : B. Kroll(Ed.). Second Language Writing (PP.140-150), 1993.

Leki, I. "Coaching from the margins: Issue in Writing Response. " In: B.Kroll(Ed.).Second Language Writing : Research insights for the Classroom.(PP-57-68), 1993.

Reid, J.M. Teaching ESL Writing. Englewood Cliffs, NJ.: Printice Hall Regents, 1993.

Rechards, J.C. The Language Teaching Matrix. Cambridge: CUP, 1990.

አባሪ 1፣ በተማሪዎች የሚሞላ የጽሁፍ መጠይቅ፣

ውድ ተማሪዎች ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቀጥታ በመመለስ ትብብር እንድታደርጉልን እንጠይቃለን፡፡ ለትብብራችሁ በቅድሚያ እናመሰግናለን፡፡

ደረጃ ገብሬና ግርማ ገብሬ

ሀ. ግላዊ መረጃ ፣

1. ጾታ--------------- 2. እድሜ ------------ 3. የአፍ መፍቻ ቋንቋ -------------------

ለ. መመሪያ፣ ከዚህ በታች ለቀረቡት ጥያቄዎች ‹‹ አዎ ›› ወይም ‹‹ አይደለም/የለም ›› በማለት በተሰጠው ባዶ ቦታ ላይ ጻፉ፤

1. በዚህ አመት በአማርኛ ክፍለጊዜ ድርሰት የመጻፍ ልምምድ አድረጌያለሁ፡፡ ---------------------------
2. ስለድርሰት አጻጻፍ የአማርኛ መምህሬ አስተምረውኛል፡፡ -----------------------
3. በዚህ አመት ድርሰት በግሌ ጽፌ አውቃለሁ፡፡ ------------------------------------
4. በአማርኛ ድርሰት የመጻፍ ፍላጎት አለኝ፡፡ ---------------------------------------
5. የድርሰት አጻጻፍ ስርአቶችን ማለትም ርእስ መምረጥ፣ ማጥበብ ፣ ማርቀቅ፣ መከለስና ማረም አውቃለሁ፡፡ -------------------------------------

እናመሰግናለን!

አባሪ 3፣ የድርሰት እርማት ውጤት

| ኮድ | አራሚ-1 | አራሚ-2 | አማካይ | ልይይት |
|---|---|---|---|---|
| ቦ-01 | 36 | 34 | 35 | 1 |
| ቦ-02 | 25 | 24 | 24.5 | 0.5 |
| ቦ-03 | 20 | 22 | 21 | 1 |
| ቦ-04 | 10 | 15 | 12.5 | 2.5 |
| ቦ-05 | 9 | 8 | 8.5 | 0.5 |
| ቦ-06 | 12 | 15 | 13.5 | 1.5 |
| ቦ-07 | 7 | 6 | 6.5 | 0.5 |
| ቦ-08 | 5 | 5 | 5 | 0 |
| ቦ-09 | 28 | 30 | 29 | 1 |
| ቦ-10 | 45 | 52 | 48.5 | 3.5 |
| ቦ-11 | 20 | 16 | 18 | 2 |
| ቦ-12 | 3 | 5 | 4 | 1 |
| ቦ-13 | 8 | 7 | 7.5 | 0.5 |
| ቦ-14 | 12 | 10 | 11 | 1 |
| ቦ-15 | 15 | 10 | 12.5 | 2.5 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ቦ-16 | 20 | 22 | 21 | 1 |
| ቦ-17 | 15 | 14 | 14.5 | 0.5 |
| ቦ-18 | 28 | 20 | 24 | 4 |
| ቦ-19 | 17 | 16 | 16.5 | 0.5 |
| ቦ-20 | 20 | 22 | 21 | 1 |
| ቦ-21 | 10 | 8 | 9 | 1 |
| ቦ-22 | 28 | 35 | 31.5 | 3.5 |
| ቦ-23 | 5 | 6 | 5.5 | 0.5 |
| ቦ-24 | 22 | 18 | 20 | 2 |
| ቦ-25 | 2 | 1 | 1.5 | 0.5 |
| ቦ-26 | 2 | 3 | 2.5 | 0.5 |
| ቦ-27 | 13 | 10 | 11.5 | 1.5 |
| ቦ-28 | 9 | 10 | 9.5 | 0.5 |
| ቦ-29 | 8 | 8 | 8 | 0 |
| ቦ-30 | 10 | 9 | 9.5 | 0.5 |
| ቦ-31 | 11 | 8 | 9.5 | 1.5 |
| ቦ-32 | 30 | 25 | 27.5 | 2.5 |
| ቦ-33 | 11 | 12 | 11.5 | 0.5 |
| ቦ-34 | 5 | 6 | 5.5 | 0.5 |
| ቦ-35 | 0 | 0 | 0 | 0 |
| ቦ-36 | 3 | 2 | 2.5 | 0.5 |
| ቦ-37 | 45 | 40 | 42.5 | 2.5 |
| ቦ-38 | 8 | 7 | 7.5 | 0.5 |
| ቦ-39 | 48 | 50 | 49 | 1 |
| ቦ-40 | 14 | 12 | 13 | 1 |
| ቦ-41 | 36 | 30 | 33 | 3 |
| ቦ-42 | 20 | 16 | 18 | 2 |
| ቦ-43 | 40 | 30 | 35 | 5 |
| ቦ-44 | 12 | 10 | 11 | 1 |
| ቦ-45 | 4 | 3 | 3.5 | 0.5 |
| ቦ-46 | 8 | 8 | 8 | 0 |
| ቦ-47 | 10 | 12 | 11 | 1 |
| ቦ-48 | 26 | 30 | 28 | 2 |
| ቦ-49 | 20 | 25 | 22.5 | 2.5 |
| ቦ-50 | 22 | 17 | 19.5 | 2.5 |
| ቦ-51 | 16 | 18 | 17 | 1 |
| አማካይ | 16.74 | 16.08 | 16.41 | 0.33 |
| ልይይት | 12.13665 | 12.09965 | 12.11815 | 0.0185 |

| ኮድ | አራሚ-1 | አራሚ-2 | አማካይ | ልይይት |
|---|---|---|---|---|
| ም-01 | 12 | 8 | 10 | 2.828427 |
| ም-02 | 20 | 15 | 17.5 | 3.535534 |
| ም-03 | 15 | 12 | 13.5 | 2.12132 |
| ም-04 | 30 | 35 | 32.5 | 3.535534 |
| ም-05 | 45 | 48 | 46.5 | 2.12132 |
| ም-06 | 18 | 15 | 16.5 | 2.12132 |
| ም-07 | 46 | 38 | 42 | 5.656854 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ም-08 | 10 | 12 | 11 | 1.414214 |
| ም-09 | 13 | 10 | 11.5 | 2.12132 |
| ም-10 | 30 | 40 | 35 | 7.071068 |
| ም-11 | 25 | 28 | 26.5 | 2.12132 |
| ም-12 | 52 | 46 | 49 | 4.242641 |
| ም-13 | 60 | 65 | 62.5 | 3.535534 |
| ም-14 | 45 | 50 | 47.5 | 3.535534 |
| ም-15 | 55 | 52 | 53.5 | 2.12132 |
| ም-16 | 58 | 55 | 56.5 | 2.12132 |
| ም-17 | 20 | 16 | 18 | 2.828427 |
| ም-18 | 43 | 50 | 46.5 | 4.949747 |
| ም-19 | 15 | 16 | 15.5 | 0.707107 |
| ም-20 | 22 | 15 | 18.5 | 4.949747 |
| ም-21 | 16 | 20 | 18 | 2.828427 |
| ም-22 | 15 | 17 | 16 | 1.414214 |
| ም-23 | 10 | 11 | 10.5 | 0.707107 |
| ም-24 | 9 | 12 | 10.5 | 2.12132 |
| ም-25 | 10 | 8 | 9 | 1.414214 |
| ም-26 | 18 | 15 | 16.5 | 2.12132 |
| ም-27 | 7 | 10 | 8.5 | 2.12132 |
| ም-28 | 23 | 25 | 24 | 1.414214 |
| ም-29 | 14 | 10 | 12 | 2.828427 |
| ም-30 | 5 | 4 | 4.5 | 0.707107 |
| ም-31 | 22 | 27 | 24.5 | 3.535534 |
| ም-32 | 8 | 7 | 7.5 | 0.707107 |
| ም-33 | 25 | 22 | 23.5 | 2.12132 |
| ም-34 | 32 | 40 | 36 | 5.656854 |
| ም-35 | 24 | 20 | 22 | 2.828427 |
| ም-36 | 10 | 12 | 11 | 1.414214 |
| ም-37 | 11 | 10 | 10.5 | 0.707107 |
| ም-38 | 28 | 25 | 26.5 | 2.12132 |
| ም-39 | 62 | 60 | 61 | 1.414214 |
| ም-40 | 45 | 50 | 47.5 | 3.535534 |
| ም-41 | 53 | 51 | 52 | 1.414214 |
| ም-42 | 40 | 46 | 43 | 4.242641 |
| ም-43 | 16 | 22 | 19 | 4.242641 |
| ም-44 | 30 | 40 | 35 | 7.071068 |
| ም-45 | 68 | 70 | 69 | 1.414214 |
| ም-46 | 42 | 52 | 47 | 7.071068 |
| ም-47 | 56 | 46 | 51 | 7.071068 |
| ም-48 | 24 | 26 | 25 | 1.414214 |
| ም-49 | 32 | 30 | 31 | 1.414214 |
| ም-50 | 36 | 42 | 39 | 4.242641 |
| ም-51 | 35 | 35 | 35 | 0 |
| ም-52 | 30 | 32 | 31 | 1.414214 |
| ም-53 | 40 | 34 | 37 | 4.242641 |
| ም-54 | 26 | 22 | 24 | 2.828427 |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ም-55 | 28 | 25 | 26.5 | 2.12132 |
| ም-56 | 35 | 30 | 32.5 | 3.535534 |
| አማካይ | 28.91071 | 29.17857 | 29.04464 | 0.189404 |
| ልይይት | 16.36213 | 17.04444 | 16.70328 | 0.48247 |